በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰበር መ/ቁ 237482

ህዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- ብሉናይል ችልድረን ኦርጋናይዜሽን ጠበቃ አለምግነት ያለው ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ታርኩ ፈይሳ ቀረቡ

ይህ መዝገብ ከሰበር መ/ቁ 237414 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የመተላለፊያ መንገድ ለማግኘት የቀረበ ክስ የሚመለከት ሲሆን መዝገቡ ለሰበር ችሎት የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል በሰበር ችሎቱ ይታረምልን በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ተጠሪ ሲሆን በመ/ቁ/ 237414 አመልካች የሆነዉ የአ/አ/ከተማ ፋይናንስ ቢሮ 1ኛ ተከሳሽ በዚህ መዝገብ አመልካች 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 የቤት ቁጥር 400 የሆነ መኖሪያ ቤት በዉርስ ያገኘ መሆኑንና በስተምስራቅ በኩል ድንበርተኛ የሆኑት ተከሳሾች ይዞታ ላይ አመልካቹ አጥር ከማጠሩ በፊት ተጠሪ ወደ ዋናዉ መንገድ መዳረሻ መንገድ አገልግሎት ሲያገኝ እንደነበር ጠቅሶ የሌሎቹ አዋሳኝ ባለይዞታዎች መኖሪያ ቤት የተገነባበት ስለሆነ መዉጫ መግቢያ መንገድ ስለሌለዉ አመልካቾች አጥር በማፍረስ መተላለፊያ መንገድ እንዲከፍቱ እንዲወስን ዳኝነት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጠይቋል፡፡አመልካቾች ለክሱ የሰጡት መልስ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ምክንያት አለመኖሩን፣ፍርድ ቤቱ ስልጣን እንደሌለዉ እንዲሁም በፕላኑ ላይ መንገድ እንደማሳይ እንዲሁም የዘጉት መንገድ እንደሌለ ገልጸዉ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ መከራከራቸዉን መዝገቡ ያሚያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካቾች በኩል የቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ በፍሬነገሩ ላይ አከራክሮና ጭብጥ መስርቶ የክፍለ ከተማ መሬትና ይዞታ አስተዳደር እና የፕላን ኮሚሽን አጣርተዉ ባቀረቡት መረጃ መሰረት ተጠሪ ቀደም ሲል በስተስሜን በኩል ከሌሎቹ ጋር ሲጠቀሙበት የነበረዉን መዉጫ የዉርስ ንብረት ክፍፍል ሲደረግ ከግምት ሳያስገቡ ባደረጉት ክፍፍል የመጣ ችግር ወይም ምክንያት አድርገዉ ተከሳሾችን የሚያስገድዱበት ምክንያት የለም በሚል ክሱን ዉድቅ አድርጓል፡፡ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የአ/አ ከተማ መሬት ልማትና ይዞታ አስተዳደር እና ፕላን ኮሚሽን በጋራ አጣርተዉ ሪፖርት እንዲያቀርቡ አድርጎ በቀረበዉ ሪፖርት ላይ በሁለቱ ይዞታ መካከል ክፍት ቦታ መኖሩን በፕላኑ ላይ ያሚያል በሚል በተጠሪ ካርታ ላይ መዳረሻ መንገድ ስለሚያሚይ የመዳረሻ መንገድ እንደነበረ በሌላ በኩል በ2010ዓ.ም በተደረገዉ ጥናት በአካል መንገድ የሌለ መሆኑን የሚገልጽ ቢሆንም ጥናቱ ተጠሪን ሙሉ በሙሉ መዉጫ መግቢያ የሚያሣጣ ሊሆን አይገባም በማለት የተከሳሾች ይዞታ ላይ ያለዉ ግንባታ ተነስቶ ለተጠሪ መተላለፊያ መንገድ እንዲከፈት ሲል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህንን ዉሳኔ ለማሳረም ነዉ፡፡አመልካቹ በቀን 19/03/2015ዓ.ም ባቀረበዉ አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ ያጋጠማቸዉ ችግር የዉርስ ንብረት ክፍፍል ሲደረግ መዉጫ ከግምት ባለማስገባታቸዉ ስለመሆኑ መረጋገጡን፣አመልካቹ ከተሰጠዉ ይዞታ ማረጋገጫ ወሰን ሳያልፍ እየተጠቀመ መሆኑን፣ለአመልካቹ በተሰጠ ካርታ ላይ መንገድ ያልተመለከተ መሆኑን፣ክፍት ቦታ የተፈጠረዉ በይዞታ መንሸራተት ስለመሆኑ የቀረበዉን ማስረጃ ወደ ጎን በመተዉ ፍርድ ቤቱ መተላለፊያ መንገድ እንደነበር ግምት መዉሰዱ የማስረጃ ምዘና ስህተት መሆኑን፣አመልካቹ የዘጋዉ መንገድ ሳይኖር ግንባታ እንዲያፈርስ መወሰኑ የፍ/ብ/ህጉን አንቀጽ1221-1223 ድንጋጌዎች የሚቃረን ስለሆነ እንዲታረም የሚል ነዉ፡፡የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ፋይናንስ ቢሮ በበኩሉ በመ/ቁ/ 237414 ላይ በቀን 16/0302015ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ አቤቱታ ለአመልካቹ በተሰጠዉ ካርታ ላይ መንገድ የማያሳይ መሆኑን፣ተጠሪ በጋራ የተሰጣቸዉ መስመር ካርታ ላይ ባለዉ መንገድ ሲጠቀሙ እንደነበር፣የአመልካች ካርታ ላይ የሚታይ ክፍት ቦታ በይዞታ መንሸራተት ምክንያት የተፈጠረ ስለመሆኑና በቅየሳ መሳሪያ ቢረጋገጥ ይሻላል የተባለዉን የባለሙያ አስተያየት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳያጣራ ማለፉ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሰበር አጣሪ ችሎት የሁለቱንም አመልካቾች አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ የያዙት ይዞታ የዉርስ ክፍፍል የተደረገበት ይዞታ እንደመሆኑ መጠን አስቀድሞ ይጠቀሙበት የነበረዉ መንገድ በሌላኛዉ የዉርስ ተጋሪ የተካለለ እና አስቀድሞ የዉርስ ክፍፍል ሳይደረግ በፊት ለግቢዉ ተጠንቶ የነበረዉ ይዞታ ላይ መንገድ እንዲወጣ በሚል የተደረሰበት ድምዳሜ እንዲሁም አስቀድሞ ተጠሪዉ ሲጠቀምበት የነበረዉን መንገድ አሁን የማይጠቀም እና መዉጫ መግቢያ ያጣ መሆኑ ጭምር የሚመለከተዉ አካል ተጠይቆ ከሰጠዉ የባለሙያ ትንታኔ አኳያ በአግባቡ ተጣርቶ የመወሰን አለመወሰኑ አግባብነት ለማጣራት በሚል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት አዟል፡፡የተጠሪ ጠበቃ መልስ ባጭሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ተጠሪ ከሌሎች ወራሾች ጋር ሲከፋፈሉ በዉርስ ያገኙት ይዞታ መከፋፈል እንደሚችል እና ከዋናዉ መንገድ መዳረሻ መኖሩን የክፍለ ከተማዉ መሬት አስተዳደር ማረጋገጡን፤ነገር ግን ይዞታ ማረጋጫ ሲሰጥ የነበረዉ መዳረሻ መንገድ ጥናት ከዓመታት በኋላ ለመንገድ የተባለዉ ቀሪ መሆኑን የክ/ከ ፕላን ኮሚሽን ምላሽ መስጠቱን፤ጥናቱ ቀርቷል ሲባል ቀደም ሲል ይህ ታሳቢ ተደርጎ የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸዉ ሰዉ መብት እንዴት ይታያል የሚለዉ እና ተያያዥ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ያለበት በአስተዳደር አካል ስለመሆኑ፤ተጠሪ ቀድሞ ሲጠቀምበት የነበረዉ መንገድ በሌላኛ ተጋሪ የተያዘ አለመሆኑን፤አሁን ይከፈትልኝ እያለ ያለዉ ቀድሞም ወደ ዋና መንገድ መዳረሻ የነበረ መሆኑንና ይህ መንገድ ቢከፈት የሚፈርስ ግንባታም ሆነ የሚደርስ ጉዳት አለመኖሩን እንዲሁም የአመልካቹ ይዞታ ማረጋገጫ የቦታ ስፋት 2482ካ.ሜ እንደሆነ በአካል የታጠረዉ ግን 2590ካ.ሜ እንደሆነ መረጋገጡንና ከዚህ አኳያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአግባቡ አጣርቶ የወሰነ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ መተላለፊያ መንገድ ያጣዉ በአመልካቹ ያልተገባ ድርጊት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የማስረጃም ሆነ የህግ ስህተት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾችም አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ፤የግራቀኙን ክርክር እና ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካላዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉ ክርክሩ የመተላለፊያ መንገድ ለማግኘት የቀረበ ክስ የሚመለከት ነዉ፡፡መሬቱ የተዘጋበት ወይም መተላለፊያ የተከለከለ ባለይዞታ የመተላለፊያ መንገድ እንዲወጣ ለመጠየቅ እንደሚችል እና መንገዱ እንዲከፈት የሚደረገዉ መተላለፊያ ያጣበት ምክንያት ከግምት በማስገባት እንዲሁም መተላለፊያ የታጠረበት እና መተላለፊያ እንዲወጣበት የተጠየቀዉ መሬት በመተላለፊያዉ መንገድ ምክንያት የሚደርስበት ጉዳት በማመዛዘን ሊሆን እንደሚገባ በፍትሓብሄር ህግ ላይ ተደንግጓል፡፡(የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1221-2223 ይመለከቷል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ መተላለፊያ መንገድ እንዲከፈትለት የሚጠይቀዉ አንድም የነበረ መተላለፊያ በሌላኛዉ ወገን ያለአግባብ የተዘጋ ሲሆን ወይም በይዞታ አጠቃቀም ለዉጥ ምክንያት

የተፈጠረ የመተላለፊያ መንገድ ችግር ካለም እንደአግባብነቱ እና አመቺነቱ ታይቶ እንደሁኔታዉ ተገቢ ካሳ ተከፍሎም ቢሆን ሌላኛዉ ወገን ይዞታ ላይ መተላለፊያ ማስከፈት የሚቻል ስለመሆኑ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ስም ተመዝግቦ በዚህ መዝገብ አመልካች እየተገለገለበት የሚገኘዉ በስተምስራቅ በኩል ከተጠሪ ጋር በሚዋሰኑበት አቅጣጫ አመልካቹ አጥር በማጠር መተላለፊያ መንገድ እንደከለከለ ጠቅሶ ግንባታ ፈርሶ መንገድ እንዲከፈትለት እንዲወሰን ተጠሪ ዳኝነት መጠየቁን መዝገቡ ያሣያል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸዉ ያጠሩት አጥር በተፈቀዳላቸዉ ይዞታ ላይ ስለመሆኑ እና የዘጉት መንገድ አለመኖሩን ይልቁንም ተጠሪ ሲጠቀምበት የነበረዉ መተላለፊያ መንገድ የተዘጋዉ የዉርስ ይዞታ ክፍፍል ጋር ተያይዞ የመጣ ችግር መሆኑን በሌላ በኩል ተጠሪ አሁንም ቢሆን ሌላ መተላለፊያ መንገድ እንዳለዉ ጠቅሰዉ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ከክሱ ፍሬነገር መገንዘብ የተቻለዉ ተጠሪ ሲጠቀምበት የነበረ መንገድ አመልካቾች ከይዞታቸዉ ጋር አጥረዉ በመያዣቸዉ ምክንያት ወይም ያለአግባብ በመጠቃማቸዉ ነዉ የተዘጋዉ የሚል ነዉ፡፡ ይህ ፍሬነገር ደግሞ በአመልካቾች በኩል ተክዷል፡፡ከዚህም በተጨማሪ አመልካቾች በይዞታ ማረጋገጫ ከተሰጣቸዉ ይዞታ ዉጪ አለመያዣቸዉንና ተጠሪ በሌላ በኩል ማለትም በስተሰሜን ባለዉ መንገድ ሲጠቅም እንደነበር እና አሁንም በዚያዉ መንገድ እየተጠየቀመ መሆኑን ገልጸዉ ያቀረቡት ክርክር መኖሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡በመሰረቱ ጭብጥ የሚመሰረተዉ ግቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በተካካዱበት የህግ ወይም የፍሬነገር ክርክር ላይ ተመስርቶ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡አመልካቾች አጥር በማጠራቸዉ መተላለፊያ መንገድ ተዘግቶብኛል ሲል ክስ ያቀረበዉ ተጠሪ እንደመሆኑ ፍሬነገሩን በቀዳሚነት የማስረዳት ሸክም የተጠሪ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2001 እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 258-259 ያሉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡በሌላ በኩል ለክሱ ምክንያት የሆነዉ የተጠሪ ይዞታ አመጣጥ ጋር በተያያዘ መነሻዉ የዉርስ ሀብት ሆኖ ከሌሎች ተጋሪዎች ጋር የተከፋፈል እና በዉርስ ያገኘ መሆኑ አላከረከረም፡፡አንድ ይዞታ በአንድ የዉል ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ በአጠቃቀም ወይም በሌላ ህጋዊ ምክንያት የወሰን ወይም አቀማመጥ ለዉጥ ከተደረገ የመተላለፊያ መንገድ ጥያቄ ሲነሳ ይህንኑ መሬት እንጂ ከዚህ ዉጪ ሊሆን እንደማይችል የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2123 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ሌላዉ የተጠሪ ክርክር እንደሚያሣየዉ የመተላለፊያ መንገድ ያጣዉ በዉርስ ክፍፍል ምክንያት አለመሆኑን ይልቁንም ቀደም ሲል ሲጠቀምበት የነበረዉን መተላለፊያ መንገድ አመልካቾች በመዝጋታቸዉ ነዉ የሚል እንደመሆኑ ይህ ስለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ከዚህ አኳያ በጭብጥነት ተይዞ መጣራት የሚገባዉ ጉዳይ፤

ሀ/ ክስ በቀረበበት አቅጣጫና ወሰን ላይ ቀደም ሲል ተጠሪ ሲጠቀምበት የነበረ መተላለፊያ መንገድ አለ ወይስ የለም? አለ ከተባለ መተላለፊያዉ አመልካቾች ያለአግባብ ባጠሩት አጥር ወይም ግንባታ ምክንያት ተዘግቷል ወይስ አልተዘጋም?

ለ/ቀደም ሲል ነባር መተላለፊያ መንገድ በሌላ ምክንያት ለዉጥ የተደረገ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ መተላለፊያ መንገድ ሊጠይቅ የሚችለዉ ከአመልካቾች ይዞታ ላይ ነዉ ወይስ ሌላ አማራጭ አለዉ ወይስ የለዉም?

ሐ/መንገዱ የተዘጋዉ አመልካቾች አለአግባብ ባጠሩት አጥር ምክንያት መሆኑ ቢረጋገጥ አሊያም ለተጠሪ ሌላ አማራጭ መተላለፊያ እንደሌለዉ የሚረጋገጥ ከሆነ ህጋዊ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለዉን ከጠየቀዉ ዳኝነት አንጻር ሊወሰን ይገባል፡፡እነዚህንና ተያያዥ ጭብጦችን በመያዝ አግባብነት ባለዉ በማስረጃ በማጣራት መወሰን ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ ጭብጥ ተይዞ ሳይጣራ መወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ሰበር ችሎቱ ስለክርክር አመራር እና ጭብጥ አመሰራረት በሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ ተገቢዉ ጭብጥ ሳይያዝና እና በተገቢዉ ማስረጃ ሳይጣራ የሚደረስ ድምዳሜ ወይም የሚሰጥ ዉሳኔ የክርክር አመራር ጉድለት ስለመሆኑ እና በሰበር ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡(ሰበር መ/ቁ/37105፣43845 እና ሌሎች መዝገቦችን ይመለከቷል)፡፡

በዚህም ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች አግባብነት ያለዉን ጭብጥ ይዘዉ ማስረጃ ሰምቶ በመሬት ላይ ያለዉን እዉነታ ማጣራትና ማረጋገጥ ሲገባቸዉ ለአመልካቾች እና ለተጠሪ በተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ላይ የመንገድ ፕላን መኖር አለመኖር ቀዳሚ ጭብጥ አድርገዉ መመርመራቸዉ የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሣያል፡፡በእርግጥ ተጠሪ ሌላ መተላፊያ መንገድ የለዉም ከተባለ ለተጠሪ የታሰበዉ የመተላፊያ መንገድ ከአመልካቾች ይዞታ ጋር የሚያያዝ መሆን አለመሆኑን እና ተጠሪ ሌላ አማራጭ የሌለዉ መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካቾች መተላለፊያ እንዲሰጡት በህግ ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩ ከላይ ተመልክተናል፡፡(የፍ/ብ/ህጉን አንቀጽ1221 ይመለከታል)፡፡ በሌላ በኩል መሬት የማስተዳደር ስልጣን የተሰጠዉ አካል በአንድ በኩል ቀደም ሲል ለተጠሪ በሰጠዉ ይዞታ ማረጋገጫ ላይ መተላለፊያ መንገድ እንደሚያሣይ እና ይህም በጥናት የተመለከተ መሆኑን እየገለጸ መልሶ በ2010ዓ.ም በተደረገ ጥናት የመንገድ ፕላን የለም ካለ ይህንን የማረም እና መፍትሔ መስጠት የሚገባዉ ይኸዉ አካል ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ በአስተዳደር አካል በኩል የሚሰጠዉ መፍትሔ መኖር አለመኖሩ በአግባብ ተሟጦ ሳይታይ አመልካቾች በአስተዳደር አካል በተፈቀዳላቸዉ ፕላን መሰረት የገነቡትን አጥር እንዲያፈርሱ መወሰኑም ተገቢነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ መተላለፊያ መንገድ እንዲከፈትለት እየጠየቀ ያለዉ ነባር መንገድ በአመልካቾች ስለተዘጋበት መሆኑን በክሱ ላይ በግልጽ ያመለከተ ስለሆነ በክሱ በተገለጸዉ አግባብ ተጠሪ ሲጠቀምበት የነበረ ነባር መተላለፊያ መንገድ በአመልካቾች ግንባታ ምክንያት ተዘግቷል ወይስ አልተዘጋም የሚለዉ እና ህጋዊ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ መመርመር ሲገባ በጥናት ለዉጥ ምክንያት ተጠሪ መተላለፊያ መንገድ ሊያጣ አይገባም በሚል ምክንያት አመልካቾች ግንባታቸዉን አፍርሰዉ መተላለፊያ መንገድ ለተጠሪ እንዲለቁ ሲል የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የክርክር አመራር ስርዓት ማለትም የጭብጥ አያያዝ እንዲሁም የማስረዳት ሸክም መርሆዎችን ያገናዘበ አይደለም፡፡የጭብጥ አመሰራረት ጉድለትም ሆነ የማስረዳት ሸክም መርህን ያላገናዘበ ክርክር አመራር መሰረታዊ የክርክር አመራር ጉድለት በመሆኑ ሊታረም የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ የስነስርዓት ጉድለት ማረም ሲገባዉ ማለፉ ተገቢ ባለመሆኑ ዉሳኔዉ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ስለሆነም ክርክሩ የተመራበት አግባብም ሆነ የተደረሰበት ድምዳሜ የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት በመሆኑ እና በዚህ ረገድ ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ገዥ ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4ሐ ና ሸ) እና 10(1/ለ) መሰረት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉሳኔ

1ኛ/የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/112368 ላይ የሰጠዉ ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/287929 ላይ የሰጠዉ ፍርድ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/235157 ላይ በቀን 08/03/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በተገለጸዉ ጭብጥ መሰረትና ተያያዥ ጭብጥ ላይ ግራቀኝ በማከራከርና አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት ተገቢዉን እንዲወስን በማለት መዝገቡን በሰበር ስነስርዓት መመሪያ አንቀጽ 9(2) መሰረት መልሰንለታል፡፡ይጻፍ

3ኛ/ሰበር ችሎቱ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትእዛዝ

1ኛ/የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ከመ/ቁ/237414 ጋር ይያያዥ ብለናል፡፡

2ኛ/ግልባጩ ለግራቀኙ የሰጣቸዉ ብለናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

3ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረዉ የእገድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ